# ´`ምዕራብ ትግራይ´´ የትግራይ መሆኑን ያረጋገጠ አዲስ የታሪካዊ ካርታ ግኝት

**ተርጓሚ፡ ነጋሲ አወጠህይ**

## Original: [Unearthed Evidence Maps out Western Tigray Dispute]


**By፡ Jan Nyssen**

**በጌንት ዩኒቨርሲቲ ቤልጅየም የፊዚካል ጂኦግራፊ ፕሮፌሰር**


በቅርብ ግዜ የተገኙ ሁለት የ19ኛዉ ክፍለ ዘመን ካርታዎች ወልቃይት የትግራይ አካል መሆኑን ያሳያሉ።




ስእል 1. ምዕራብ ትግራይ በሀንድቴክ ካርታ

ምዕራብ ትግራይ እጅግ ከፍተኛ የጦር ወንጀሎች (war crimes) ና የብሄር ማጽዳት (ethnic cleansing) ወንጀሎች የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሁም የአማራ ክልል መንግስት ታሪካዊ የአማራ መሬት ነዉ በማለት በሀገ ወጥ መንገድ በስሩ ማድረጉን የትኩረት ቦታ እንዲሆን ችለዋል።

በኢትዮጵያ ሕገ መንግስት መሰረት ክልሎች የተዋቀሩት በታሪካዊ ግዛትነት (historical administrative arrangements) ሳይሆን ቋንቋን ና ብሄርን (linguistic settlement patterns) መሰረት በማድረግ ነዉ። በዚህም መሰረት ምዕራብ ትግራይ ፍጹም አብዛኝዎቹ ነዋሪዎች (predominant residents) ነባር ትግርኛ ተናጋሪዎች (native Tigrigna speaking) በመሆናቸዉ ትግራይ ተብሎ እንዲካለል ሆኖዋል።

ይሁን እንጂ ብዙ የአማራ ብሄርኞች እና ርስት አስመላሾች (nationalist irredentists) በታሪክ የአማራ በመሆኑ ይዘዉት እንደሚገኙ ይገልጻሉ። ይህ ታሪክን መሰረት ያደረገ ባለቤትነት (historical ownership) አብዛኛዉን ኢትዮጵያ ክፍል የሚደግፈዉ አሁን ያለዉን የፌድራል አስተዳደር አወቃቀር የጣሰ ከመሆኑም በተጨማሪ አሳማኝ የታሪክ መረጃና ማስረጃ ማቅረብ አልቻሉም።

ገና ከጅምሩ ጀምሮ ለትግራይ ጦርነት እንደ ኢንጅን ሆኖ ያገለገለዉ የአማራ ርስት ማስመለስ ፖለቲካ (Amhara irredentizm) ነዉ። ጦርነቱ እንደተጀመረ የፍልምያ አዝማምያ ሲቀየርም መሬት ላይ ሲሆን እንዳየነዉ ወድያውኑ ምዕራብ ትግራይ ብቁጥጥራቸዉ ስር አደረጉት። ይሄም በግልጽ የሚያሳየዉ እና የሚያረጋግጠዉ ርስት ማስመለስ (ለም መሬት መወሰድና) የትግራይ ክልልን ማጥፋት (subjugation)) የጦርነቱ ዋና ዓላማና ስትራተጂ እንደነበረ ነዉ።

እንደማረጋግጫ የሚሆነን የትግራይ ሀይሎች መቐለን መልሰዉ ከተቆጣጠሩት በሁዋላ አንድ የመንግስት ደጋፊ July 2021 በኩራትና ራስ መተማመን `` ተዋቸዉ ይሂዱ! የተጨናገፈቺዉ ታላቋ ትግራይ በ1990ዎቹ ከአማራ የሰረቀቻቸዉ ለም መሬቶች ጥላ ወደ አለታማ ትግራይ ትሂድ....ትግራይ አሁን የቀረ ዘመናዊ እርሻ ኢንዱስትሪም መሰረተ ልማትም የላትም ፤ሁሉም ወድሟል`` ያለዉን ነዉ።

የብዙዎቻችንን ቀልብ የሳበዉ April 13/2022 በርሊን መቀጫዉ ያደረገዉ የአፍሪካ ቀንድ አጥኚዎች ቡድን (scientific working group horn of Africa) ባዘጋጀዉ ኮንፈረንስ በፕሮፌሰር ዎልበርት ስሚዝ የቀረበዉ ጽሁፍ ነበር። ጽሁፉም ምዕራብ ትግራይ የጎንደር አካል ነው የሚለዉን ትርክት የሚያፈርስና የሚጻረር አዲስ የካርታ ግኝት ይዞ መምጣቱ ነበር።

ከዚህ ኣጋጣሚ በሁዋላ ባደረግነዉ የጠለቀ አሰሳ ምዕራብ ትግራይ በግዜው የትግራይ አካል መኖሩን የሚያሳዩ ብዙ የ19ኛዉ ክፍለዘመን ኢጋማሽ ካርታዎች አግኝተናል።

የዚህ ጽሁፍ አላማ የድንበር ክርክርን ከተገኙት ካርታዎች በመነሳት ብያኔ ለመስጠት አይደለም። ይልቅንስ የ ሲ ኤፍ ዊላንድ 1841 እና ኤፍ ኤች ሀንድቴክ 1849 ዓ/ም እ.ኤ.አ እንደ ታሪካዊ ካርታነታችዉ እና መዛግብትነታችዉ ፋይዳችዉ ለማሳየት እንዲሁም የግዛትና ድንበር አወቃቅርና አከላለል እጅግ ተለዋዋጭ እና ውስብስብ እንደነበረ ለማሳየት ነው።

በሌላ አነጋገርም በአማራ ወገን የሚቀርበዉ የርስት ባለቤትነት ትርክት የአንድ ወገን ብቻና አሳማኝ ማስረጃዎችን ያልቀረበበት መሆኑንም በደንብ መገንዘብ ያስፈልጋል። ያም ሆነ ይህ ግን የድንበርና መሬት ባለበትነት ይገባኛል ርቱዕ የሚሆነዉ ክርክሮችም እልባት ማግኘት ያለባቸዉ በታሪክ ባለቤትነት ክርክር ሳይሆን አሁናዊ እዉነታን በአጽናኦት በመዉሰድ (should reflect current realities) ነዉ መሆን ያለበት፡፡

## የሀንድቴክ ካርታ

የሃንድቴክ ካርታ ግዙፍና ብዙ ዝርዝር ቦታዎችን የያዘ ቢሆንም በዚህ ጽሁፌ ያተኮርኩት በአትላስ ማተሚያ ቤት በ19ኛዉ ክፍለ ዘመን አጋማሽ የታተመዉ የሀንድቴክ (1849) ካርታ ነዉ። ካርታዉ 39 ሴ.ሜ ስፋት እና 66 ሴ.ሜ ቁመት ያለዉ፤ ስኬሉም 1:5,600000 ነዉ፤ ከፍታማ ቦታዎችን ና መልካአ ምድሮችንም በካርታዉ ተመላክተዋል።

የ19ኛዉ ክፍለ ዘመን መጀመርያና አጋማሽ ገደማ የዲፕሎምሲና ሌሎች ምንጮች እንደሚጠቁሙት ካርታዉ የተመረተዉ በዘመኑ ይደረግ እንደነበረዉ በሊቶግራፊክ ህትመት እና ማኑዋል አወት ላይን ከለሪንግ (lithographic printing with manual outline coloring) ነው።

ካርታዉ የተሰራዉ በ19ኛዉ ክፍለ ዘመን በጀርመን ከነበሩት ጥቂት ግን ደግሞ ታዋቂ ህትመት ቤቶች አንዱ የሆነዉ የካርል ፍሌሚንግ (1806-1879) የካርቶግራፊክ ህትመት ቤት ነው። ካርቶግራፈር ፍሬድሪክ ሃንድቴክ (1815-1879) በፍሌሚንግ ሀትመት ካርታ ስራዎች ተባባሪ ሆኖ ይሰራ የነበረ የካርታ ጠቢብ ነዉ።

## ሰሜናዊ የምስራቅ አፍሪካ በ1849

ካርታዉ የሚያሳየዉ ጂኦግራፊ የቀይ ባህር ዳርቻ፡ ግብጽና ``ኑብያ`` እንዲሁም የሰሜናዊና ማእከላዊ ኢትዮጵያ ደጋማ አካባቢዎችን ነው። ይሄም በጉልህ የሚያሳየዉ የ``ትግራይ`` ``አማራ`` እንዲሁም ወደ ደቡብ ደግሞ በደበዘዘ ንድፍ ቢሆንም እስከ ሸዋ (Schoa) ድረስ ይዘልቃል። የካርታ ሰሪዎቹ ዓላማ የነበረዉ እነዚህን ማሳየት ነው።

የሰሜናዊ የደጋማ አካባቢ በተሻለ አኩሁን ካርታ የተሰራለት ቢሆንም የራሱ ችግርም አለበት። ለምሳሌ በቀጥታ ወደ ተከዘ የሚፈሰዉ አረቋ (Areqwa) ወንዝ በስሀተት በተከዜ ትየዩ እንደሚፈስ እና ከሌሎች ገባሮች ጋር ለምሳሌ ከእነ ግባ (Giba) እና ወርዒ (Werií) ወንዞች ጋር እንደሚገናኙ ተድርጎ ተቀምጦዋል።

በሩቅ ደቡብ አቅጣጫ ኢናርያ (Enaria) ዲስቺማ (Dschimma) እና ካፋ (Kaffa) ግልጽ ባልሆነ ደረጃ ካርታዉ ላይ ተቀምጦዋል። የወል የሚመሰል (generic name) ህበሾች (Habesch) የሚል ስም በደጋማዎቹ (highlands) መሰመሮች በአግድም ተቀምጦዋል።

የ19ኛዉ ክፍለ ዘመን የሰሜናዊው ምስራቅ አፍሪካ ካርታዎች ሰለ ስነ-መካን (toponyms) ማለትም የቦታ ስሞች (place names) የስፋፊ ግዛቶች ስም (regional names) ሀዝቦች የሚኖሩበት የመሬት ቆዳ (territorial extent) እንዲሁም

የአካባቢዎቹ ድንበሮችና መንገዶች እውቀት፤ የተደራረቡ የፖለቲካ ታሪኮች የብሄር ግጭቶችንና ግንኙነት በተመለከት ብዙ መረጃ የሚሰጡ ናቸዉ።

በሌላ አገላለጽ ካርታዎቹ የካርታ ሰሪዎችና ተመራማሪዎች ዉጤት ብቻ ሳይሆኑ አገርና አካባቢ በቀል እዉቀትና የዛ ዘመን እውነታን ማለትም የግዛት፡የመሬትና ማህበረ ፖለቲካዊ እዉቀት ካላቸዉ የአገርና አካባቢ አዋቂዎች ጋር በነበረዉ ሂደታዊ ግንኙነት የተመረተ የጋራ ውጤት ነው።




*ስእል 2. ሀበሻ "Habesh" እንደ ህንድቴክ 1849 ካርታ*

በሀንድቴክ ካርታ ራስ ዓሊ በአብዛኛዉ ማእከል አድርጎ ይዞት የነበረዉ ``አማራ`` በአብዛኛዉ የአሁኑ አማራ ክልል ነዉ። ወሎ ግን የተለየ ሌላ ግዛት ነበር። የትግራይ ግዛት ደግሞ የኤርትራ ደጋማ አካባቢዎች (``Bahrenegash``) እና የአሁኑ ትግራይ ክልል በምዕራብ በኩል ያለዉ ወልቃይት (walkayt) ና ዋልድባ (walduba) ን ጨምሮ ያካተተ ማለት ነው።

አገሩ በአጠቃላይ እንደ ጸና አገር ሳይሆን (unified ``country``) መቆጠር የለበትም:: ለየት ባለ መልኩ ግን የትግራይ ግዛት የራስ ገዝ ቅርጽ (confederate-style structure) የነበረዉ ከስሩም ከፊል ነጻ የሆኑ ግዛቶች (provinces and princedoms) የነበሩት በደጃት ዉቤ ግዜ በተሻለ ደረጃ ወደ አንድ ግዛትነት ቅርጽ የመጡበት አጋጣሚ ነበር። በግዛቶች ወይም አውራጃዎች (provinces) መካከል ወንዞች በተለይ በዝናብ ወቅት የወንዝ ሙላት እንደ እንቅስቃሴ አጋች ሆኖ ግዛቶቹ በታላቁ የትግራይ ማእቀፍ ዉስጥ ከፊል ራስ ገዝ እንዲሆኑ አስተዋጸኦ አድርጎዋል ።

ካርታዉ በተስራበት ግዜ 1849 ዓ/ም እ.ኤ.አ ኤርትራ ራስዋን እንደቻለች ግዛት አልተካተተችም፤ ኤርትራ የተፈጠረቺዉ በኮሎንያል ግዛት ከሃንድቴክ ዘመን በሁዋላ ስለሆነ። ካርታዉ ላይ ከሀበሻ (Habesh) በስተ ምዕራብ ያለዉ ቆላማዉ አካባቢ በግልጽ አይታይም ነገር ግን `ሻንቅላ` (Schangalla)፡ ቆላ መዘጋ (Kolla Mazaga) ወይም ዳአር ኤል በርታ (Dar El Berta) በስም ደረጃ ተካተዋል።

## አሁን ስላለዉ ክርክር (current disputes)

ከእነ ሀንድቴክ እና ቁላንድ በፊት ሪጎበርት ቦኔ የተባለ ካርታ ሰሪ አንድ ያነሰ ጥራትና ግልጽነት ያለዉ የትግራይ ራስ ገዝ ካርታ (outlines of confederate Tigray) ሰርቶ ነበር።

እነዚህ ካርታዎች አቻምየለህ ታምሩ ወልቃይት የአማራ ነዉ ብሎ ለማስረጽ በጻፈዉ ስብስብ ወይም መጽሀፍ ሆነ ተብለዉ ከተተዉ ብዙ ታሪካዊ ካርታዎች ወስጥ ናቸዉ። በተጨማሪም ወልቃይት የትግራይ ታሪካዊ መሬት መሆኑ የሚጠቅሰዉ ``walakayit in Tigray`` የታዋቂዉ ሪቻርድ ፓንክረስት (1990) መጽሓፍ በጸሃፊዉ አቻምየለህ ሆነ ተብሎ ተትቶዋል።

እነዚህ ካርታዎች የሚሳያዩት በመጀመርያዎቹ ና አጋማሽ 20ኛዉ ክፍለ ዘመን ከነበረዉ አዲስ የግዛት አወቃቀር በስተቀር ወልቃይት ሁሌ የበጌ ምድር ፕሮቬንስ አካል (አሁን በአማራ ክልል አስተዳደር ያለው) ነበረ የሚለዉ የአማራ ብሄርተኞች ትርክት የታሪክ ማስረጃ ላይ ያልተመሰረተ መሆኑን ነዉ።

እዉነት ነዉ፤ የአቢሲንያ አጼዎች ዳግማዊ ምኒሊክና ቀዳማዊ ሃይለስላሴ የአገሪቷን ህዝብና መሬት ከፋፍለዉት የነበረዉ በፕሮቬንስ (provinces) ነዉ። ማለትም ከዘመናቸዉ በፊት ከፊል ራስ ገዝነት የነበራችዉ ግዛቶችን ቀያይሮዋቸዋል።

የኮሎኒያል ገዢዎች በሌሎች ሀገሮች ላይ እንዳደረጉት በተመሳሳይ ቀዳማዊ ሀይለስላሴ ከዛ ዘመን በፊት የነበሩ ነባር ግዛቶች (territories) እንደ አዲስ በመሸንሸን (territorial re-organization) ለምስለኔዎቻችዉ በሽልማትና ገጸ በረከት መልኩ አከፋፍለዉታል። በዚያ ዘመን መስተዳድር ግዛቶች ሲመሰረቱ በጂኦግራፊያዊ ማእከልነት (strength of local powers) እንጂ በብሄር (ethnic composition) አልነበረም።

በአንጻሩ ደግሞ ወደ ምራብ ትግራይ ስንመለስ፡- በትግራይ ወገን ያለዉ ቅቡል ባለበትነት የሚመነጨዉ አሁን ካለው በ1995 ዓ/ም እ.ኤ.አ የተፈጠረዉ የፌደራል አወቃቀር ነዉ። አሁን ያለዉ የትግራይ ክልል እንደሌሎች ክልሎች የተፈጠረዉ በህገ

መንግስቱ መሰረት በመሆኑ፡- ክልሉ ሲዋቀር ራስን በራስ የማስተዳደር እና ቋንቋ ብሄር ይዘትና አሰፋፈርን መሰረት በማድረግ እንጂ በዋናነት ታሪካዊ ካርታን መሰረት በማድረግ አልነበረም።

በግልጽ እንደሚታየዉ ሁሉም ታሪካዉያን የቋንቋ ስርጭት ጥናቶች (all language maps) አሁን ያለዉን የትግራይ ክልል ተብሎ የተካለለዉ በብሄርና ቋንቋ ይዘቱ ስናይ በዘላቂነት የትግርኛ ተናጋሪዎች (ተጋሩ) መሆኑን ያሳያል። ለምሳሌ ለመጥቀስም፡- የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ካርታ በJ. Spencer Trimingham የተሰራዉ ካርታ በሁዋላ በ Egbert Westphal በ1975ዓ/ም እ.ኤ.አ በድጋሜ የታትመዉ ማየት ይቻላል። የእነ J. Spencer Trimingham እና Egbert Westphal የቋንቋ ስርጭት ካርታዎች ሲሰሩ ጥቅም ላይ የዋሉት ድንበሮች (boundaries) በ1960ዎቹ ና በ1970ዎቹ እ.ኤ.አ መጀመርያ በነበሩት ፕሮቬንሥስ (provinces) መሰረት ነው። ከ1994 ዓ/ም እ.ኤ.አ በሁዋላ ያለዉ ካርታ የትግራይ ክልል ትግርኛ ተናጋሪ ኢትዮጵያን ብቻ ያካትታል። ምክንያቱም ኤርትራ ነጻ ህገር ሆናለች።




ስእል 4. ምዕራብ ትግራይ በብዛት የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ትግረዎት መሆኑ የሚያሳይ ካርታ

ታሪካዊ ካርታዎች የEthiopian Map Research Project የምርምር ትኩረት አዉዶች በመሆናቸዉ በዚህ ላይ በኢትዮጵያ ደጋማዉና ሰሜን አካባቢ ካርታዎች ላይ እየሰራ ያለዉ ፕሮፌሰር ዎልበርት ስሚዝ በተለይ የ19ኛዉ ክፍለ ዘመንን በተመለከተ አዳዲስ የካርታ ግኝቶችን እንደሚያወጣ ይጠበቃል።

## ለማጠቃለል

ለማጠቃለል ይህ የታሪካዊ ካርታዎች ጥናት (historical cartography) ´`ወልቃይት የአማራ ርስት ነው ትግራይ ሆኖ አያውቅም`` የሚለዉ ረዘም ላለ ግዜ የተስተጋባዉ የአማራ ርስት አስመላሾች ትርክት ከእዉነት የራቀ ያደርገዋል። በታሪክ ባለቤትነት ከሆነ ሙሉ የባለቤትነትና የግዛት የሺ ዘመናት ታሪክ ማወቅን ይጠይቃል። በተጨማሪም ለዚህ የመሬት ውዝግብ የሚበጅ መፍትሄ በመሰረታዊነት ከ1991 እና 2020 በፊት የነበረዉ የብሄርና ቋንቋም ሁኔታ (ethno-linguistic situation) እዉነታ አጉልቶ ማሳየት መቻል አለበት።